# ምርጫ 2002 የሕዝቡ ትክክለኛ ውሳኔ የሚከበርበት፣ ሰላማዊና ፍትሃዊ ምርጫ ሊሆን ይገባል!

## ከኢዴፓ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የተሰጠ መግለጫ

የኢትዮጵያውያን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኢዴፓ) ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ለሰላማዊ ትግልና ለምርጫ ፖለቲካ ያለውን ቁርጠኝነት በተግባራዊ ተሳትፎ ሲያሳይ ቆይቷል፡፡ ኢዴፓ የአገራችን የወደፊት ዕጣ-ፈንታ ሊወሰን የሚገባው በሰላማዊ ትግልና በህዝብ ምርጫ ብቻ ነው ብሎ ስለሚያምን ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ በ2002 በሚካሄደው አገራዊ ምርጫ ለመሳተፍ ወስኗል፡፡ የወቅቱ የአገራችን የፖለቲካ ምህዳር የቱንም ያህል ችግሮች ያሉበት ቢሆንም እነዚህን ችግሮች ለመፍታትም ሆነ በችግሮቹ ውስጥ አልፎ የተሻለ ውጤት ለማምጣት የሚቻለው ራስን ከምርጫ ሂደት በማግለልና አኩራፊ በመሆን ሳይሆን አቅምና ሁኔታ በፈቀደ መጠን ተሳትፎ በማድረግ መሆኑን በማመን ኢዴፓ በመጪው ምርጫ ለመሳተፍ ከመወሰንም አልፎ በምርጫው ጠንካራ ተፎካካሪ ሆኖ ለመቅረብ የሚያስችለውን ዝግጅት ከወዲሁ በተጠናከረ ሁኔታ በመላው አገሪቱ ጀምሯል፡፡

የኢዴፓ 4ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ በወሰነው መሰረት ኢዴፓ በመጭው አገራዊ ምርጫ ቢያንስ 75 በመቶ የሚሆነውን የአገሪቱን የምርጫ ክልሎች ሸፍኖ ለውድድር ለመቅረብ ዝግጅት የጀመረ ሲሆን ምርጫውን አስመልክቶ በሚካሄዱ የውይይትና የክርክር መድረኮችም የጎላ ሚና ለመጫወት የሚያስችሉትን ዝግጅቶች በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ምርጫ 97ን ተከትሎ በአገራችን በተፈጠረው የፖለቲካ ቀውስ ምክንያት የኢዴፓ የትግል እንቅስቃሴ አስቸጋሪ ሁኔታ ገጥሞት የነበረ ቢሆንም ይህ አስቸጋሪ ሁኔታ ከአለፉት ሁለት አመታት ጀምሮ በከፍተኛ ፍጥነት እየተለወጠና እየተቃለለ መጥቷል፡፡ እንዲያውም ካለፈው የፓርቲው 4ኛ ጠቅላላ ጉባኤ በኂላ ፓርቲው በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች እያደረገ የሚገኘው እንቅስቃሴ የበለጠ እየተጠናከረና አበረታች የሆነ የህዝብ ድጋፍ እያገኘ መጥቷል፡፡ ቀደም ሲል በኢዴፓ ላይ በተካሄደው የተቀነባበረ ያሉባልታ ዘመቻ ምክኒያት ከፓርቲው ለመራቅ ተገደው የነበሩም በርካታ አባላቱም በሂደት እውነቱን በመገንዘብ በፓርቲው ዙሪያ እንደገና መሰባሰብ ጀምረዋል፡፡

በኢዴፓ እምነት ይህ ዓይነቱ በጎና አበረታች ሁኔታ በፓርቲው ዙሪያ በአሁኑ ወቅት እየተፈጠረ የመጣው ያለ ምክንያት ሳይሆን በአንድ በኩል በምርጫ 97 ወቅት በቅንጅት ዙሪያ ተፈጥሮ ለነበረው ቀውስ ምክንያቱና መንስኤው ማንና ምን እንደነበረ ጊዜና ሂደት ለህዝቡ በቂ መልስ እየሰጡ በመምጣታቸው ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ፓርቲው በአሁኑ ወቅት እያራመደው የሚገኘው የ3ኛ አማራጭነት የፖለቲካ ስልት በሂደት በህዝቡ ዘንድ እየታወቀና ተቀባይነት እያገኘ በመምጣቱ ነው ብሎ ያምናል፡፡ ይህ የፓርቲያችን ተቀባይነት ለመጪው ምርጫ ከሚዘጋጁት የተለያዩ የክርክር መድረኮችና ፓርቲው ከሚያካሂደው አጠቃላይ የምረጡኝ ዘመቻ ጋር ተያይዞ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ይሸጋገራል የሚልም እምነትና ግምት አለን፡፡

በአሁኑ ወቅት ፓርቲያችንን አስመልክቶ በህዝቡ ዘንድ እየተፈጠረ ከመጣው በጎ አመለካከት በተጨማሪም በኢዴፓና በገዢው ፓርቲ መካከል በፖለቲካና በኢኮኖሚ ፕሮግራሞች እረገድ ያለው ልዩነት ከሌሎች ፓርቲዎች ልዩነት በበለጠ በጣም ሰፊና መሰረታዊ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በሁለቱ ፓርቲዎች መካከል ቀደም ሲል የነበረው ውጥረትና መፋጠጥ የበዛበት ግንኙነት ግን በሂደት ወደ ጤናማ የፖለቲካ ተቀናቃኝነት ስሜት የመሸጋገር በጎ አዝማሚያ ማሳየት ጀምሯል፡፡

በአሁኑ ወቅት በፓርቲያችን እንቅስቃሴ ላይ በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች እየደረሱ የሚገኙ ችግሮችን ከገዢው ፓርቲ አመራሮች ጋር በመነጋገር የመፍታት ጥረት እየተደረገ ሲሆን ሂደቱ ወደፊትም በዚሁ ከቀጠለና ጤናማ ግንኙነቱ በአመራር ደረጃ ብቻ ሳይሆን በሁለቱ ፓርቲዎች የበታች አባላትና ደጋፊዎች መካከልም እየተጠናከረ መምጣት የሚችል ከሆነ እንዲህ አይነቱ ግንኙነት ለአባሎቻችንና ለደጋፊዎቻችን ደህንነት ዋስትና የሚሰጥ ከመሆኑም በላይ በአጠቃላይ መጭውን ምርጫ ነጻና ፍትሃዊ ከማድረግም ሆነ ለአገራችን የፖለቲካ ባህል መዳበር የማይናቅ አስተዋፅኦ ከማበርከት አኳያ የሚኖረው ሚና ከፍተኛ ይሆናል። ይህም ፓርቲያችን ኢዴፓ ከሌሎች ፓርቲዎች በተለዬ በአሁኑ ወቅት እያራመደው ከሚገኘው የ3ኛ አማራጭነት የትግል ስልት ጋር ተያይዞ እየመጣ ያለ በጎ ለውጥ ነው የሚል እምነት አለን።

በተመሳሳይ ሁኔታ በአሁኑ ወቅት ሶስት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከገዥው ፓርቲ ጋር በምርጫ ጉዳዮች ዙሪያ እያካሄድነው የሚገኘው ድርድር ከጠበቅነው በላይ አበረታች ውጤት ማሳየት ጀምሯል። በድርድሩ ላይ ቀዳሚ አጀንዳ ሆኖ በቀረበው የፓርቲዎች የሥነ-ምግባር ደንብና የደንቡ የማስፈፀሚያ ስልት ላይ ከገዢው ፓርቲ ጋር ስምምነት ላይ መድረስ ተችሏል።ይህ የአራቱ ፓርቲዎች ስምምነትም የበለጠ ዳብሮና ተሻሽሎ በአገሪቱ በሚገኙ በሌሎች 65 ፓርቲዎች ተቀባይነት አግኝቷል። ከዚህ ስምምነት የመነጨው ረቂቅ ሰነድም በቅርብ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቅርቦ እንደሚጸድቅ የታወቃል። በዚህ ስምምነት መሰረትም በምርጫ የምንፎካከር ፓርቲዎች እርስ በርሳችን ተከባብረንና የአገሪቱን ህጎች አክብረን በምርጫው ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለመወዳደር፣ በማንኛውም የፓርቲ አባልም ሆነ የምርጫ ተወዳዳሪ እጩ ላይም ምንም አይነት ጫናና የአፈና ድርጊት እንዳይፈፀም፣ ይህን የፓርቲዎች የሥነ-ምግባር ደንብ ጥሶ የተገኘ የተቃዋሚዎችም ሆነ የገዢው ፓርቲ አባልና ደጋፊም በህግ ተጠያቂ እንዲሆን የሚያስችል ስምምነት ላይ መድረስ ተችሏል።

ይህ በአገራችን ተፎካካሪ ፓርቲዎች መካከል ለመጀመሪያ ጊዜ የተደረገ ታሪካዊ ስምምነት በሁሉም ተፎካካሪ ፓርቲዎች ተቀባይነት ካገኘና በተግባር ከዋለ፣ በተጨማሪም በቀጣይ ለድርድር በሚቀርቡ ተመሳሳይ አጀንዳዎች ዙሪያ ተመሳሳይ ስምምነት ላይ መድረስ የሚቻል ከሆነ ድርድሩ መጭውን ምርጫ ነፃና ፍትሃዊ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል ብሎ ኢዴፓ ያምናል። ይህ በአገራችን ፖለቲካ ኃይሎች ድርድር ወደፊት ለድርድር በተያዙ አጀዳዎች የበለጠ ውጤታማ ይሆን ዘንድም ኢዴፓ በድርድሩ ሂደት እስከመጨረሻው ለመዝለቅና ለምርጫው ውጤታማነት የበኩሉን በጎና ግንባር ቀደም አስተዋፅኦ ለማበርከት ከልቡ እየሰራ ይገኛል። ተደራዳሪ ፓርቲዎች ስምምነት ላይ የደረሡበትን የምርጫ የስነ-ምግባር ደንብም ካለፈው ዕሁድ ጥቅምት 29 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ አበባ ለሚገኙ አባላቱ የማሳወቅና የማስተማር ስራ ጀምሮል።

ኢዴፓ በዚህ ሁኔታ ሙሉ ትኩረቱን በምርጫ ዝግጅት ላይ አድርጎ እየሰራ ቢሆንም አንዳንድ ፓርቲዎችና የህብረተሰብ ክፍሎች ከምርጫ 97 በፊት በነበሩት ዓመታት በሰፊው ይሉት እንደነበረው ዛሬም መጭው ምርጫ ውጤታማ እንደማይሆን አስቀድመው በመገመት በምርጫው ዙሪያ ፓርቲዎችም ሆኑ ህዝቡ የሚኖራቸውን ተሳትፎ የሚያጣጥል አቋም ሲያራምዱ እየታዩ ነው። በኢዴፓ እምነት የወቅቱ የአገራችን የፖለቲካ ምህዳር የቱንም ያህል በችግሮች የተሞላ ቢሆንም መጭውን ምርጫ ከወዲሁ ማጣጣልና ራስንም ሆነ ህዝብን ከምርጫው ሂደት ለማግለል መሞከር ካለፉት ስህተቶቻችን መማራችንን የማያሳይ ዳግም ታሪካዊ ስህተት ይሆናል።

ከመጭው የምርጫ ሂደት በአኩራፊነት ራስን ማግለል ለተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ ለህዝቡም ሆነ በአጠቃላይ ለአገራችን የዴሞክራሲ ሂደት ጉዳት እንጂ ምንም አይነት ጥቅም የሚያስገኝ

ውሳኔ አይሆንም፡፡ በኢዴፓ እምነት ራስን ከምርጫ ሂደት በማግለል ውሳኔ የሚጠቀም ኃይል አለ ከተባለ ያ-ኃይል ማንም ሳይሆን በእጁ የመንግስት ሥልጣን ይዞ የሚገኘውና የአገዛዝ እድሜውን ለተጨማሪ 20 እና 30 ዓመታት ለማራዘም አቅዶ እየሰራ የሚገኘው ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ ብቻ ነው፡፡ በተለይም ተቃዋሚ ፓርቲዎች ገዥውን ፓርቲ የጎዳን መስሎን በመጭው ምርጫ ምንም አይነት ውጤትና ለውጥ እንደማይገኝ አድርገን በመቀስቀሳችን ምክንያት በመጭው ምርጫ የፓርቲዎችም ሆነ የህዝቡ ተሳትፎ ቀዝቃዛ የሚሆን ከሆነ ተቃዋሚዎች ተጠናክረን ለፖለቲካ ስልጣን የምንበቃበትም ሆነ ህዝቡ ከኢህአዴግ አገዛዝ የተሻለ አማራጭ የሚያገኝበት ጊዜ የበለጠ የተራዘመ እንደሚሆን በመገንዘብ የተሳሳተ ስልታችንን ከወዲሁ በማስተካከል በመጭው ምርጫ በከፊል ሳይሆን በሙሉ ልባችን ተሳታፊ መሆን ይገባናል፡፡

የተቃዋሚ ፓርቲዎች ደጋፊ የሆነው የህብረተሰብ ክፍልም ምርጫ ዘጠና ሰባትን የኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ሂደት መጀመሪያና መጨረሻ አድርጎ ከማየት የተሳሳተ አመለካከት በመውጣት በመጭው የ2002 ዓ.ም ምርጫ ከ 97 ዓ.ምቱ ምርጫ የተሻለ ውጤት ለማምጣት ከወዲሁ መዘጋጀትና መረባረብ ይኖርበታል፡፡ ህዝቡ ዛሬም ሆነ ነገ በሰላማዊ ትግልና በምርጫ ሂደት ለውጥ ሊያመጣ እንደሚችል በሙሉ ልቡ ተማምኖ ተሳትፎ እስካደረገ ድረስም የሌሎች አገሮች የታሪክ ሂደት እንዳረጋገጠው በእኛም አገር እውነተኛ የህዝብ ድምፅ የበላይነቱን የማያረጋግጥበት ምንም ዓይነት ምክኒያት አይኖርም፡፡ የህዝብ ድምፅ የበላይነቱን ሳያገኝ ሊቀጥል የሚችለው በአገራችን የጥላቻ፣የተስፋ መቁረጥና የአኩራፊነት በአጠቃላይ የዜሮ ድምር ፖለቲካ ቦታ እግኝተው እስከቀጠሉ ድረስ ብቻ ይሆናል፡፡

ኢዴፓ ከዚህ ፅኑ እምነት በመነሳት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በመጭው ምርጫ በሙሉ ልቡ ተሳታፊ ለመሆን ወስኗል፡፡ ከመወሰኑም በላይ በአሁኑ ወቅት በአብዛኛው የአገሪቱ ክፍሎች ተግባራዊ የምርጫ ዝግጅት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ የአገሪቱ የወቅቱ የፖለቲካ ምህዳር ስፋትና ጥበት ምንም ይሁን ምን፣ የወቅቱ የፖለቲካ ድርጅቶች ድርድር የመጨረሻ ውጤት ምንም ይሁን ምን ኢዴፓ ማቄን ጨርቄን ሳይል በመጭው ምርጫ ተወዳድሮ ውጤት እንደሚያመጣ ከወዲሁ እርግጠኛ በመሆኑ ለምርጫው የሚያቀርባቸውን እጩዎች የመመልመል ስራ በመላው አገሪቱ በሰፊው ጀምሯል፡፡

ኢዴፓ ምን ያህል በነፈሰበት የማይነፍስ የአቋም ፓርቲ እንደሆነና በያዘው የ3ኛ አማራጭነት የፖለቲካ ስልትም አባላቱንና ደጋፊዎቹን ተፈላጊ ላልሆነ መስዋእትነት የማይዳርግ ኃላፊነት የሚሰማው ምክንያታዊ ፓርቲ መሆኑን በመገንዘብ ሕዝቡ በዙሪያው ተሰልፎ የበለጠ ሊያጠናክረው ይገባል፡፡ ፓርቲያችን በአሁኑ ወቅት እያራመደው ከሚገኘው የምክኒያታዊነት ፖለቲካ፣ በዚህም ምክኒያት ከመቻቻልና ዕውቅና ከመስጠት የሠለጠነ የፖለቲካ አካሄድ ጋር በተያያዘ ከገዢው ፓርቲ ጋርና ከሌሎች በርካታ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር እየፈጠረ ከመጣው ገንቢ አመለካከትና በአሁኑ ወቅትም ስምምነት ከተደረሠበት የፓርቲዎች የስነ-ምግባር ደንብ አኳያ ከእንግዲህ አባሎቻችንና ደጋፊዎቻችን ከማንኛውም የተጽዕኖና የአፈና ድርጊት ነጻ ሆነው ያለምንም ስጋት የዕለት ተዕለት ስራቸውን እየሠሩና ቤተሰባቸውን እያስተዳደሩ የፖለቲካ አቋማቸውን በሰላም የሚያራምዱበት ሁኔታ እየተጠናከረ መምጣቱን ህዝቡ ሊገነዘብ ይገባል፡፡ ሕዝቡ ይህንን እውነታ ተገንዝቦ በዙሪያችን እስከተሰለፈ ድረስም በወደፊትዋ ኢትዮጵያ ኢህአዴግን ሰላማዊና ህጋዊ በሆነ መንገድ አሸንፎ መንግስታዊ ስልጣን ለመያዝ የሚችለውም ሆነ የሚገባው የኢዴፓ የ3ኛ አማራጭነት አመለካከት ነው የሚል ከፍተኛ ተስፋና እምነት አለን፡፡

ስለሆነም ሰላማዊ ትግልና የምርጫ ፖለቲካ በአገራችን ተጠናክሮ ለውጤት እንዲበቃ ፍላጎት ያለው ኢትዮጵያዊ ሁሉ ይህንን የኢዴፓ ወቅታዊ አቋም በውል በመገንዘብ በሁለንተናዊ መልኩ ማለትም የፓርቲ አባል በመሆን፣ የምርጫ እጩ ተወዳዳሪ በመሆን፣ የቁሳቁስ፣ የገንዘብና የሃሳብ ድጋፍ በማድረግ የበኩሉን አስተዋፅኦ እንዲያበረክት በዚህ አጋጣሚ ፓርቲያችን ጥሪውን ያቀርባል፡፡

**ሠላምና ህብረ-ብሔራዊነት ዓላማችን ነው!**

**ኢዴፓ-የወደፊቱ ፓርቲ!**

**ሕዳር 3 ቀን 2002 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**